# የ2001 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

ፈጣንና ቀጣይነት ያለውን ልማት ለማምጣትና ከልማቱም ህብረተሰቡ ሙሉ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ሥርዓት ለመዘርጋትና መልካም አስተዳደር የሰፈነበት ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት የማስፈጸም አቅም ግንባታ ተግባራት ወሳኝነት አማራጭ የለውም፡፡ ይህንን በመገንዘብ የሁሉም ተቋማትን የማስፈጸም አቅም ቀጣይነት እንዲኖረው ለማስቻል በተከታታይ መሠራት እንዳለበት ታምኖ እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በ2001 በጀት ዓመትም በዋናነት የሲቪል ሰርቪስ ፕሮግራሞችንና ያልተማከለ የወረዳ አስተዳደርን እንዲሁም የመልካም አስተዳደር ፓኬጅን መሬት ለማስረገጥ ታቅዶ እንቅስቃሴ ሲደረግ ቆይቷል፡፡

## *1. በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ትግበራ ዘርፍ:-*

- በሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራሞች ልዩ ትኩረትና ቅድሚያ የተሰጠው ለመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናትና ትግበራ ሲሆን በ2000 በሙከራ ትግበራ ወቅት የተገኙ ማሻሻያና የማስተካከያ ግብዓቶችን በማካተት በዞናችን በጥር 2001 ወደሙሉ ትግበራ ለመግባትና ለውጡን ከዞናችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ለማዛመድ በሚያስችል መልኩ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ሙሉ ትግበራ ለማስጀመር ይቻል ዘንድ በዞኑ ሁሉም ሴክተሮች 225 ወንዶችና 84 ሴቶች በአምስቱ ወረዳና ከተማ አስተዳደር 899 ወንዶችና 206 ሴቶች በጠቅላላ ድምር 1124 ወንዶችና 290 ሴቶች አጠቃላይ ድምር 1414 ሠራተኞች ፤ኃላፊዎችና አመራር አካላት ሁለት ዙር የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡
- ሴክተር መ/ቤቶች ለትግበራው ስኬት ዝግጅት :-የቢሮ አደረጃጀት፤ቁሳቁስና መገልገያ መሳርያዎች፡በኢኮቴ መሳሪያዎች ማደራጀትንና በተሟላ ብቁ የሰው ኃይል ሁሉ አቀፍ ቅድመ ዝግጅት ድጋፍና ክትትል ተደርጓል፡፡ከዚህም ጋር ተያይዞ የመንግስት መ/ቤቶች ያለባቸው የሰው ኃይል ዕጥረት እየተፈተሸ በልዩ ልዩ ሙያ ከመንግስትና ከግል ተቋማት የተመረቁ ባለሙያዎች ቅጥር የተከናወነ ሲሆን በሰርተፍኬት መምህራን 60 ወንድ 47 ሴት ድምር 107፣ዲፕሎማ መምህራን 27 ወንድ 26 ሴት ድምር 53፣ዲግሪ መምህራን 31 ወንድ 1 ሴት ድምር 32 በአጠቃላይ በትምህርት መስክ 118 ወንዶችና 74 ሴቶች በድምሩ 192 ተቀጥረዋል፡፡ በግብርና መስክ 5 ወንዶች 1 ሴት ድምር 6 በሌሎች ሴክተር መ/ቤቶች 18 ወንድ 5 ሴት በድምሩ 23 በጠቅላላው 141 ወንዶችና 80 ሴቶች ድምር 221 በወረዳ ከተማ አስተዳደርና ዞን ማዕከል ተደልደለው የሲቪል ሰርቪስ አገልግሎቱን ለማሻሻልና ለማቀላጠፍ ጥረት እየጠደረገ ይገኛል፡፡
- በዞኑ የሚተገበረውን የ BPR ሙሉ ትግበራ አፈጻጸም ህብረተሰቡ እንዲያውቀው ለማድረግ በቴሌቪዥን ፕሮግራም፣ የኢትዮጵያ ሬድዮና ደቡብ FM 100.9 የአየር ሽፋን ተሠጥቷል፡፡
- በዞኑ በሚገኙ ሁሉም ተቋማት ለ BPR ትግበራ የሚያገለግሉ ደንብ 72/2001ና ሌሎችም ተያያዥ መመሪያዎች ስርጭት ተከናውኗል፡፡

- ለሙሉ ትግበራ በተመረጡ 7 ሴክተር መ/ቤቶች የሠራተኞች ድልድል ተካሂዶ በዞን ማዕከል 130 ወንዶችና 40 ሴቶች በድምሩ 170 በተርጫ ከተማ 45 ወንዶች 16 ሴቶች ድምር 61 በአምስቱ ወረዳ 465 ወንዶችና 94 ሴቶች በድምሩ 559 በአጠቃላይ ድምር 640 ወንዶችና 150 ሴቶች በጠቅላላው 790 የተደለደሉ ሲሆን ፤ለውድድር ቀርበው ከነበሩት 125 ወንዶች 24 ሴቶች በድምሩ 149 ሠራተኞች መካከል በትምህርት ዝግጅት ማነስ፤145 ሠራተኞች፤ ከ50% በታች ውጤት በማምጣት 3 ሠራተኞች፤ በትምህርት መስመር ያለመገናኘት 1 ባጠቃላይ 149 ምደባ አላገኙም፡፡ ይሁን እንጂ የዞኑ የመፍትሄ አማራጮች አስተግባሪ ግብረ ኃይል በየጊዜው ባደረጋቸው ስብሰባዎች 32 ሠራተኞች በሚያሟሉት የሥራ ዘርፍ በዞን ሴክተር፣ ከተማ አስተዳደርና ወረዳዎች ምደባ ሲሰጣቸው ፤ከነዚህ ውጭ የሆኑት፤ 20 ለረዥም ጊዜ ስልጠና፤ 66 ለማቋቋምና ፤31 ለጡረታ ተለይተው በድምሩ 117 ሠራተኞች መረጃቸው ለክልሉ አቅም ግንባታ ቢሮ ተልኳል፡፡
- በየደረጃው የሚገኙ ኃላፊዎች፣ፈጻሚዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በሴክተሩ የለውጥ ተቃውሞ አያያዝና አመራር ላይ ተገቢውን ሚና እንዲጫወቱ የሚያስችል አጠር ያለ ጽሁፍ/ብሮሽር/ተዘጋጅቶ ተሰራጭቷል፡፡
- የአቅም ግንባታ መምሪያን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ለህዝብ ይፋ ከማድረግ አኳያ " ስኬት" የተሰኘ ዓመታዊ መጽሔት ተዘጋጅቶ ተሰራጭቷል፡፡
- የድጋፍና ክትትል ተግባራትን ከማጠናከር አኳያ ለሴክተሮች ፣ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደር የግምገማ ግብረ መልስ የሚሰጥበት የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡
- የቢሮ ዝግጅትን በተመለከተ የነበራቸውን ግድግዳ በማፍረስ በወረዳ ፋ/ኢ/ልማት ጽ/ቤቶች፣ፖሊስ በወረዳና ዞን የተደራጁ ሲሆን፤ ባሉበት ሆነው የሥራ ቦታ ያደራጁ የዞን መምሪያዎች ግ/ገ/ልማት፣ትምህርት፣ስራና ከተማ ልማትና ንግድና እንዱስትሪ መምሪያዎች ናቸው፡፡ የዞኑ አቅም ግንባታ መምሪያ በዞን አስተዳደር ድጋፍ የራሱ ቢሮ ተከራይቶ የተደራጀ መሆኑ ይጠቀሳል፡፡ይሁን እንጂ በጥቂት ወረዳዎች የቢሮ አደረጃጀቱ ያልተጠናቀቀና በሂደት ላይ የሚገኝ ሲሆን በተወሰኑ ወረዳዎች የቢሮ ግንባታዎች በአፋጣኝ እየተካሄዱ ናቸው፡፡

➢ የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራን በተመረጡት ሴክተር መ/ቤቶች በመገኘት፡-

❖ የተደለደለው የሰው ሃብት በተጠናው መሰረት መሆኑን
❖ በየሥራ ሂደቶቹ የቲም ቻርተር ዝግጅት ተከናውኖ መፈራረማቸውን
❖ በየሳምንቱ የትግበራ አፈጻጸም ውይይት እየተካሄደ መሆኑን
❖ ፈጻሚዎች ውሳኔ ሰጪ መሆናቸውን
❖ ሴክተሩ እስከታችኛው እርከን ድረስ በቼክ ሊስት የተደገፈ ድጋፍ ማድረጋቸውን
❖ የቀድሞ አስተሳሰቦች እየተቀረፉ በአዳዲስ አሰራሮች እየተተኩ መሆናቸውን
❖ አገልግሎት አሰጣጡ በአፈጻጸም ስታንዳርድ እየተመዘገበ ከቀድሞ የተሻለ ውጤት እየታየ መሆኑን

- ❖ አስተባበሪዎችና ፈጻሚዎች በአንድ ክፍል ውስጥ ተግባራቸውን እየፈጸሙ መሆናቸውን
- ❖ የአገልግሎት አሰጣጥ ቅድመ ሁኔታ ለተገልጋይ ግልጽ መሆኑን በሩብ ዓመት አንድ ጊዜ የድጋፍና ክትትል ተግባራት ተከናውነዋል፡፡
- ❖ በተጨማሪም ወደሙሉ ትግበራ ያልገቡ ስምንት ሴክተር መ/ቤቶች ለትግበራው የሚያደርጉትን ቅድመ-ዝግጅት ከወዲሁ እየተከታተልንና አስፈላጊ ግብዓቶችን በማቅረብ በተቋም ፣በአመራርና በአገልጋይ ዘንድ ሊፈጠር በሚገባው የግንዛቤ ማስጨበጥ ተግባራት ላይ ያላሰለሰ ርብርብ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡
- ❖ በለውጥ ፕሮጀክቶች ፕሮግራም ጥናትና ትግበራ የሥራ ሂደትና አስተግባሪ ሴክተሮች መካከል የአፈጻጸም ክትትልና ድጋፍ ውል ስምምነት መፈራረምና በየሳምንቱ በተቋም ደረጃና በሥራ ሂደት ደረጃ የሚታዩ የአፈጻጸም ግድፈቶችና ችግሮች ላይ በመወያየት ድጋፋዊ ክትትል እየተደረገ መሆኑና አበረታች ውጤቶች መታየታቸው ሳይጠቀስ አይታለፍም፡፡
- ❖ ይህ ወደሙሉ ትግበራ የተገባውና ትልቅ ለውጥ ያመጣል ተብሎ የታመነበት ጥናት የአመለካከት ለውጥ መጥቶ ወደማይቀለበስበት ደረጃ እስኪደርስ ድረስ ብርቱ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ለዚህም ስኬት ሁሉም በየደረጃው የሚገኙ አካላት ድጋፍና ክትትል እንዲሁም ሚናቸውን በብርቱ መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

*ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፡-*

- ➢ ትምህርታቸውን በማሻሻል የደመወዝ ለውጥ የሚጠይቁ ባለሙያዎች የሚያቀርቧቸው አቤቱታዎች፤
- ➢ የዓቃቤያነ ህግ የደመወዝ ጭማሪ የፈጠረው ቀውስ፤
- ➢ የሰው ኃይል ዕጥረት መከሰት/በተለይም በኢኮቴ የሥራ ዘርፍ፡/፤
- ➢ የኢኮቴ መሳሪዎች በተፈላጊው ደረጃ ያለመሟላት፤
- ➢ እገዳው ባልተነሳበት ሁኔታ ዝውውርና የደረጃ ዕድገት ሊከናወን የነበረ መሆኑ

## *2. በመልካም አስተዳዳር ፓኬጆች ትግበራ፡-*

- ፈጣን ልማትን በማምጣት የህዝብ ተጠቃሚነትን እውን ከማድረግ አኳያ የመልካም አስተዳደር ፓኬጅ አፈጻጸምንና የምርጥ ተሞክሮ ቅመራን በአሰተባባሪና ቴክኒክ ኮሚቴዎች ሙሉ እውቀት ተፈጥሮ ወደ ስራው በመገባት ምርጥ ቀበሌዎችን፤ ምርጥ ወረዳዎችንና ሞዴል አርሶ አደሮችን በመምረጥ የምክርና ቴክኒካል ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡በተጨማሪም በወረዳና ዞን ሴክተር መ/ቤቶች አገልግሎት አሰጣጥ ላይም የምርጥ ተሞክሮ ቅመራ ተግባራት የተከናወኑ ሲሆን ሴክተሮች ደረጃ ወጥቶላቸው እንዲያወቁት ተደርጓል፡፡ በዚህም ምክንያት ከፌዴራል አቅም ግንባታ የተላኩ ባለሙያዎች በዞኑ የምርጥ ተሞክሮና መልካም አስተዳደር ጋር ተያይዞ ያደረጉት ቅኝት አበረታችና የሰጡትም አስተያየት የበለጠ እንድንሰራ የሚያደርግ እንደሆነ ሳይጠቀስ የማይታለፍ ነው፡፡

- በዘመኑ የመኸርና በልግ ወራት ምርትና ምርጥ ዘር እንዲሁም ግብዓት፤ በማስፋት ሥራ እየታገዘ ከመጠን በላይ የተሳካ ውጤት እንዲያስመዘግብ ሁለገብ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ከዚህም ጋር ተያይዞ በየቀበሌው የተቋቋሙት የልማት ኮሚቴዎች በመቀናጀት አሳታፊ የልማት ተግባራትን ህ/ሰቡን በማሳመን እያስፈጸሙ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም ተሳትፎአዊ የልማት ተግባራት መካከል የዳውሮ ባህልና ታሪክ ቅርስ ምርምር ማዕከል ዋናውና ተጠቃሹ ነው፡፡
- በዞናችን በሚገኙ 170 ቀበሌያት የተመደቡ ሥራ አስኪያጆችን የተሃድሶ ስልጠና ከመስጠት አንጻር ለሶስት ተከታታይ ቀናት በመልካም አስተዳደር፤አገልግሎት አሰጣጥ፤ የማስፋት ተግባራት ድጋፍ፤ የፕሮጄክት አቀራረጽና አቀራረብ፤ የልማት ዕቅድ አወጣጥ በመሳሰሉት ርዕሶች ሥልጠና ተሰጥቷቸዋል፡፡
- በገጠር ቀበሌዎችና ከተማ አስተዳደር የቀበሌ ሥራ አስኪያጆች የህዝብ አስተያየት መስጫ መዝገብና ሣጥን፤ የጉዳይ መቀበያ ፎርምን በመጠቀም ምርታማነትን ከማሳካት አንጻር በአጭር ጊዜ ተገልጋዩን ያረካ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ድጋፍና ክትትል እየተደረገ ሲሆን፡የቀበሌውን ዓመታዊ የልማት ዕቅድ በማስተቸት፤ የመሰብሰቢያ አዳራሾችን በመገንባት ፤ጽ/ቤቶችን በማሠራት የልማቱን እንቅስቃሴ ህብ/ሰቡን በማሳመን ተግባራዊ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

## 3. የፍትህ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራሞች፡-

- በዞናችን የፍትህ ሥርዓቱን ተደራሽ ለማድረግና ከመሰረቱ ለማሻሻል ይቻል ዘንድ የፍትህን ተደራሽነት፤ ቀልጣፋነትና ፈጣንነት ውጤታማ ለማድረግ በዞን በወረዳና በቀበሌ የፍትህ ስ/ማ/ፕሮ/አስተባባሪና የቴክኒክ ኮሚቴዎች ተቋቁመው የዓመቱን ዕቅድ አዘጋጅተው እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ፡፡በተጨማሪም በፍትሕ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራሞች ሥር የተጠቃለሉት ሴክተሮች የካናወኗቸው ተግባራ ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

- ምክር ቤት፡-
    - የዞን የወረዳና ከተማ አስ/ረ ምክር ቤቶች የፍትህ ሥርዓቱን ለመደገፍ ፤የሰው ኃይል ምደባ እንዲሁም የቋሚ ኮሚቴ እንቅስቃሴን በመምራት ፍትህን ተደራሽና ቀልጣፋ ለማድረግ እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ፡፡
    - የፍትህ ሥርዓት አስተባባሪና የቴክኒክ ኮሚቴዎች በፕሮግራማቸው መሰረት እየተሰባሰቡ የዕቅድ ግምገማ በማካሄድ በዞን ምክር ቤት የሚገኙ ቋሚ ኮሚቴዎችም የፕሮጄክት ግምገማ በማድረግ ላይ ሲሆኑ ለ21 የዞን ቋሚ ኮሚቴ አባላትና ምክር ቤት ባለሙያዎች እንዲሁም ለ28 ዋናና ምክ/አፈ ጉባዔዎች የአቅም ማጎልበቻ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

- ፍርድ ቤቶች :-
  - የፍርድ ሥርዓትን ቀልጣፋ በማድረግ ጉዳዮች በተገልጋዩ መኖርያ ወይም አቅራቢያ ለማድረግ በዞኑ ባሉት አምስት ወረዳዎች በየሩብ ዓመት የተዘዋዋሪ ችሎቶች የሚሰየሙ ሲሆን የወረዳ ፍርድ ቤቶችም በአጠቃላይ ድምር 17 ሥፍራዎች ላይ የተዘዋዋሪ ችሎት ጣቢያዎችን በማቋቋም አገልግሎት እየተሰጠ ቢሆንም በተመረጡት ሥፍራዎች አዳራሾች ቢሮዎችና የዳኞች ማረፊያ ሥፍራ ያልተመቻቸ በመሆኑ የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት ተጽዕኖ ማሳደሩ ተደርሶበታል፡፡
  - በወረዳዎች የሚታየውን የጉዳይ ክምችት ለማቃለል የከፍተኛ ፍ/ቤት ዳኞች ወርደው የሚደግፉ ሲሆን ይኸው ተግባር ግን የራሱ የሆነ ደካማ ጎን እንዳለውም ተረጋግጧል፡፡
  - በዞን ደረጃ የተከላካይ ጠበቃ መቀጠሩ፤
  - በተጨማሪም አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓት በዕድሮች ፣በማህበረሰብ ውይይቶች ጭምር መታየቱ በፍርድ ቤቶች ላይ የሚታየውን መረጃ የማጣራት የሥራ ጫና በመቀነሱ ሊበረታታ የሚገባው ነው፡፡
  - ለማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞችና ሬጅስትራሮች የንቃተ ህግ ማሻሻያ ሥልጠናዎች መሰጠታቸው፣ ት/ቤቶችንም በመጠቀም በቅንጅት የሚሰጠው የንቃተ ህግ ትምህርቶች በተከታታይ መሰጠታቸው፣ተጠቃሽ ናቸው፡፡
- የዓቃቤ ህግ ማሻሻያ
  - የፍትህና የጸጥታ ችግሮችን ከህብረተሰቡ ጋር በመቀናጀት በተለይም ከፖሊስ ጋር ባለው የሥራ ትብብር ህብረተሰቡን በማስተማር፣በተፈጠሩ ችግሮች ምክንያት የተንዛዛ ቀጠሮ በማይታይበት ሁኔታ አገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡
  - የህግ ባለሙያዎችን ዕጥረት ለመቅረፍ ከዞን አስተዳደር በተሠጠ ልዩ ትኩረት በተቻለ መጠን ከገበያ ላይ ብቃት ያላቸው የህግ ባለሙያዎችን በመቅጠር የተሰራው ተግባር ቀላል የማይባል ነው፡፡
  - በተለይም የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራ መነሻ በማድረግ ትምህርታቸውን ያሻሻሉ በመርማሪ ከሳሽ ንዑስ የሥራ ሂደት ላይ ምደባ ያገኙና ተጨማሪ የሰው ኃይል ቅጥር በማከናወን ለዘርፉ በተሰጠው ትኩረት የክስ አቀራረብ ግድፈቶች እየታረሙ የተሻለ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡

- በተጨማሪም በሃሰት መስካሪዎች ላይ የሚደረገው ማጣራትና ውሳኔ በህዝብ ግንኙነት ለህብረተሰቡ ይፋ የሚደረግበት አሠራር ቢዘረጋ ከዚህ አጉል ልምድ ጋር ተያይዞ የሚባክነውን የአርሶ አደሩን ወረቃማ የሥራ ጊዜ ባግባቡ ለመጠቀም ያስችላል ተብሎ ይታመናል፡፡

- የፖሊስ ማሻሻያ፡-
  - ወንጀል ከተሠራ በኋላ ለማጣራት የሚደረገው ውጣ ውረድ ከመከላከል ጋር ሲታይ እጅግ አድካሚ በመሆኑ የዞናችን ፖሊስ በመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራ በወንጀል መከላከል የሥራ ሂደት ላይ ያለውን የሰው ኃይል በማስለፍ ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ ይገኛል፡፡
  - በዞኑ የሚገኙ ከ170 ቀበሌያት በላይ የፖሊስ ኃይሉ ቀበሌዎችን ደርቦ በመያዝ የመከላከል ተግባራትን እያከነወኑ የሚገኙ ሲሆን በአብዛኛው በቀበሌው ህብረተሰብ ትብብር የተከሰቱ ወንጀሎች እዛው ተጣርተው የሚቀርቡበት ሁኔታ ተጀምሯል፡፡
  - በቅርቡ የሰው ኃይል ምደባ የተካሄደበት የመርማሪ ከሳሽ ንዑስ የሥራ ሂደት ቢዘገይም ከመከላከል የሥራ ሂደት ጋር የተዘረጋው ቅንጅታዊ አሰራር ይበልጥ ሊበረታታ የሚገባው ሲሆን አሁን በመከላከል ላይ የተመደበው ኃይል ተጨማሪ የሰለጠነ የፖሊስ ኃይል ሊመደብለት የሚገባው መሆኑ ሊተኮርበት ይገባል፡፡
  - በመርማሪ ከሳሽ የሥራ ሂደት እንዲሁም ወንጀል መከላከል የሥራ ሂደቶች በቅንጅት የሚሰሩበትና በንቃተ ህግ ትምህርት ህብረተሰቡ ዕውቀቱን ለማሻሻል የተጀመሩ ተግባራት መኖራቸው፣በሚመለከተው ወገን ድጋፍ ሊደረግለት ያሻል፡፡

- የማረሚያ ቤቶች ማሻሻያ፡-
  - የታራሚዎችን ሰብዐዊ መብት ከማስጠበቅ ጀምሮ ታራሚዎች በማረሚያ ቤት የሚያገኟቸው አገልግሎቶች የተሟሉ እንዲሆኑ የሚደረገው ጥረት እንዳለ ሆኖ የማምለኪያ ስፍራዎች መዘጋጀታቸው፣የህክምና አገልግሎት በተቋሙ ቅጥር ውሥጥ ማግኘታቸው ጥሩ ጅምር ሲሆን ከመጸዳጃ ና የልብስ ንጽህና አገልግሎት ጋር ተያይዞ የሚታየው ችግር ትኩረት የሚሻ ነው፡፡
  - የማረሚያ ተቋማችን ከታራሚዎች ዝንባሌ ጋር ተያይዞ የማምረቻና ማሰልጠኛ ማዕከል ለማድረግ በማረምና ማነጽ የሥራ ሂደት በብረታብረት ሥራ ፣ልብስ ስፌትና ሽመና እንዲሁም በእንጨት ሥራ ለማሰልጠንና ታራሚዎች ከማረሚያ በሚወጡበት ጊዜ በዕውቀታቸው ህ/ሰባቸውን ሊያገለግሉ የሚችሉበትን ሁኔታ ለማደራጀት የባለሙያ ቅጥር መጀመሩ፣በፍትህ ዘርፍ የታዩ ስኬቶቻችን ናቸው፡፡

*4. በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ፡-*

- በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍም ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓትን ለማጠናከርና ባለሙያው ዘመኑ ባፈራቸው የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች እንዲጠቀም ለማስቻል

- 49 ወንዶችና 6 ሴቶች በድምሩ 55 ባለሙያዎችና አመራር አካላት በኢንተርኔት አጠቃቀም ለአንድ ወር ሥልጠና መሰጠቱ፤
- 58 የሎማ ወረዳ ግብርናና ገ/ልማት ባለሙያዎች በቪዲዮ የተደገፈ የተፋሰስ ልማት ስልጠና መውሰዳቸው፤
- የፕሪፓራቶሪ ተማሪዎች የሰሩዋቸውን የጥናት ሰነዶች ለሀርለም የሳይንስ አካዳሚ/HARLEM SCINCE ACADAMY/ በኢ-ሜይል እንዲልኩ መደረጉ፤
- 9 የፎቶ ኮፒ ማሽኖች፤ 4 ኮምፕውተሮች፤ 1 ፋክስና 1 ፕሪንተር ባለሙያ በመጥራት በብር 4900.00 ጥገና መካሄዱ፤
- በፕላዝማ ብልሽት ምክንያት ትምህርት ማግኘት ላልቻሉ የሁለተኛ ደ/ት/ቤቶች ከክልሉ በተገኘ የባለሙያ ድጋፍ ጥገና ተደርጎ የፕላዝማ ስርጭት እንዲያገኙ መደረጉ፤

በአጠቃላይ በዞናችን የማስፈጸም አቅም ግንባታ ስትራቴጂና ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ለማድረግ ትክክለኛ አቅጣጫ ይዘን እየተጓዝን ሲሆን ፕሮግራሞቹ ረጅም ጊዜ የሚጠይቁና ተከታታይነት ባለው ሁኔታ መፈጸም ያለባቸው መሆኑ ግንዛቤ ተይዞ በየደረጃው የአመለካከት ለውጥ እንዲመጣና የተጀመሩ የአሰራርና የአደረጃጀት ለውጦች ይበልጥ እንዲጠናከሩ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችና ባለድርሻ አካላት ርብርብ ፤እንዲሁም በየእርከኑ የሚገኙ አካላት ድጋፍና ክትትል ወሳኝነት ይኖረዋል፡፡

# የ2002 በጀት ዓመት ዕቅድ

በዞናችን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ልማት ለማምጣትና ከልማቱም ህዝቡን በላቀ ደረጃ ተጠቃሚ ለማድረግ እንዲቻል አሁንም በየደረጃው የሚታዩትን የማስፈጸም አቅም ችግሮችን ደረጃ በደረጃ ለመፍታ ማቀድ ወሳኝነት አለው፡፡ በዚሁ መሰረት በ2002 የበጀት ዓመት የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ትግበራን በአዳዲስ አሰራር፣ አደረጃጀትና በበቃ የሰው ሃብት ልማትና አመራር በመታገዝ በዘመናዊ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በማሳለጥና በማቀላጠፍ ተቋማዊ ለውጥ ( Organizational Transformation) እውን ማድረግና በመልካም አስተዳደር እመርታ ማምጣት ቁልፍ የትኩረት መስክ ሆኖ ታቅዷል፡፡

በዚህ መሰረት መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናቱን የተሟላ ለማድረግ በአዲስ መልክ የሚጠኑ የጥናት ውጤቶችን ከዞኑ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማስማማት አሠራሩን ሥራ ላይ ለማዋል ታቅዷል፡፡ በሁሉም የመንግስት ተቋማት የተጠናከረና ተከታታይነት ያለው ድጋፍና ክትትል በማድረግ መሠረታዊ

የሥራ ሂደት ለውጡን የመተግበሩ ሥራ ተቋማዊ መልክ እንዲይዝ ይደረጋል፡፡ በዞኑ በሚገኙ በሁሉም የመንግስት ተቋማት ሚዛናዊ የውጤት ተኮር ዕቅድ አሠራር በመዘርጋት ለመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ተቋማዊ መልክ መያዝ የተመቸ ሁኔታ የመፍጠርና የማትጊያ ሥርዓቱን የመትከል ሥራዎች በበጀት ዓመቱ የሚከናወኑ ይሆናል፡፡

በመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ የግብርናና ገጠር ልማት፣የሥራና ከተማ ልማት እና የንግድና ኢንዱስትሪ ተቋማት እመርታዊ ለውጥ እንዲያመጡ ከማድረግ አንጻር ልዩ የሆነ የማስፈጸም አቅም ግንባታ ድጋፍ ለማድረግ የታቀደ ከመሆኑም በላይ በሁሉም የአስተዳደር እርከኖች ለሚሰሩ አመራሮች ፣ባለሙያዎችና ሠራተኞች በፖሊሲዎችና የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጽንሰ ሃሳብ ላይ ስልጠናና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፡፡

የአስቀጣይ ተቋማትን የማስፈጸም አቅም ማሳደግ፣በመልካም አስተዳደር ፓኬጅ አፈጻጸም እመርታዊ ለውጥ ማምጣት ፣በዞኑ በሁሉም ወረዳዎችና ቀበሌዎች የእንስፔክሽን አደረጃጀትና አሠራር በመዘርጋት አጠናክሮ ሥራ ላይ ማዋል በበጀት ዓመቱ ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚከናወኑ ተግባራት ናቸው፡፡

በሁሉም ቀበሌዎች የቀበሌ መዋቅርን አሳምኖ ማሰራትን በማጠናከር የተቀመሩ ምርጥ ስኬቶችን የማስፋፋት ሥራዎች በትኩረት የሚከናወኑ ሲሆን በሁሉም የገጠር ቀበሌዎቻችን የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ በተጠናከረ መዋቅር እንዲሰራ ቀጣይነት ያለው ክትትልና ድጋፍ በማድረግ አሁን የሚታየውን ክፍትት የመሙላት ሥራ የዕቅዳችን ሌላው አካል ነው፡፡በሁሉም የመንግስት ተቋማት የተገልጋዮች ቅሬታ የሚስተናገድበትን አሠራር በመዘርጋትና ሥራ ላይ በማዋል የሚቀርቡ ቅሬታዎችንና ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮችን በአግባቡ በመፍታት እና ለከተማ መልካም አስተዳደር ፓኬጅ አፈጻጸም ድጋፍ ለመስጠት ታቅዷል፡፡

በተጨማሪም በፕሮግራሞቻችን የአፈጻጸም ስኬቶችና ጉድለቶች ላይ የፋይዳ ጥናት የሚካሄድ ከመሆኑም በላይ በሁሉም የፍትህ ስርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም ተደራሽነት፣ውጤታማነትና ቀልጣፋ እንዲሆን በማድረግና በሁሉም የዞኑ ቀበሌያት የኮሙኒቲ ፖሊሲንግ ሥርዓት በመዘርጋት ረገድ ድጋፋዊ ክትትል ይደረጋል ፡፡

በዞኑ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎትን የማስፋፋትና አዲስ የመዘርጋት የቪዲዮ ኮንፍረንሲንግ የሚሰጥባቸውን ወረዳዎችና ቀበሌዎች የማደራጀትና የዞኑን የመንግስት ሠራተኞች መረጃ በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ለማደራጀት ታቅዷል፡፡

## ማጠቃለያ

በ2002 ዓ.ም የበጀት ዓመት በቁልፍ የትኩረት መስክ የተያዘውን መልካም አስተዳደርን የማስፈንና ዴሞክራሲን እውን የማድረግ ትልማችንን በመምታት በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ በማሳለጥ በፈጣን አገልግሎት አሰጣጥ የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥን ማሳካት የመጀመሪያውና አማራጭ የማይገኝለት የትኩረት አቅጣጫችን ነው፡፡